# ቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ

# የመጀመሪያ ዲግሪ የመዉጫ ፈተና ማስፈፀምያ አጭር መዋቅራዊ መመሪያ

ህዳር፤ 2015 ዓ.ም
ቀብሪደሃር ዩኒቨርቲ

© ቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ

2022/23 የትምህርት ዘመን

ይህ መመሪያ ምንም እንኳን ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት ቢሆንም በየጊዜዉ እንደአስፈላጊነቱ ስለሚሻሻል በሚያነቡበት ወይም በሚተገብሩበት ወቅት ያገጠሞትን ይህ ቢጨመር ወይም ቢቀነስ የሚሉት ሀሳብ መመሪያዉን በየጊዜዉ ለማጎልበት ስለሚረዳ እንዲለግሱን እየጠየቅን፤ ያላግባብ የተተረጎመ ወይም ከት/ት ሚኒስቴር የመዉጫ ፈተና መመሪያ ጋር የሚጣረስ ቃል ወይም ዓረፍተ ነገር ካለ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሚሻሻል ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

**Contact:**

**Name: Kibebew B. (MSc, Asst. Professor)**

**E-mail:-Kibebew86@gmail.com**

**Inst. E-mail:- kibebewbabege@kdu.edu.et**

**Telegram/Imo/WhatsApp:- +251930522554**

# ማዉጫ

**ይዘት** **ገፅ**


መግቢ ........ 2
1. ምዕራፍ አንድ ........ 3
1.1 የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ ሟቋቋም ........ 3
1.2 የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ አብይ ኮሚቴ ትርጉም ........ 3
1.3 የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት ........ 4
2. ምዕራፍ ሁለት ........ 6
2.1 የኮሌጅ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም ........ 6
2.2 በኮሌጅ ደረጃ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ትርጉም ........ 6
2.3 በኮሌጅ ደረጃ የሚቋቋመዉ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት ........ 6
3. ምዕራፍ ሶስት ........ 8
3.1 የት/ት ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም ........ 8
3.2 በት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ትርጉም ........ 8
3.3 የት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት ........ 8
4. ምዕራፍ አራት ........ 11
4.1 የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም ........ 11
4.2 የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ትርጉም ........ 11
4.3 የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት ........ 12
5. ምዕራፍ አምስት ........ 13
5.1 የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም ........ 13
5.2 የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል የመዉጫ ኮሚቴ ትርጉም ........ 13
5.3 የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት ........ 14
6. ምዕራፍ ስድስት ........ 15
6.1 ማጠቃለያ ........ 15

# መግቢያ

የቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ በ 2010 ዓ.ም አዳዲስ ከተከፈቱ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ከመሆኑ አንፃር እስካሁን ባለዉ ሂደት 1433 ተማሪዎችን አስተምሮ ያስመረቀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በመደበኛ እና በሳምንቱ መጨረሻ በቅድመ እና በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ከ 5000 በላይ ተማሪዎችን እያስተማረ ይገኛል፡፡ ተቋማችን ከተደራሽነት በተጨማሪ የትምህርት ጥራት ላይ በአበክሮ እንዲሰራ እና ዉጤት እንዲመጣ በፅኑ ያምናል፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን የሚጠበቅባቸዉን ብቃት ያሟሉ መሆናቸዉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኑ በመገኘቱ፤በአገራዊ እና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ምሩቃንን በሁሉም የትምህርት መስኮች ለማፍራት እንዲቻል፤እንዲሁም ከአካባባዊ፤አገራዊና አለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ፤የቴክኖሎጂ እድገትና ከማህበረሰቡ ፍላጎት ጋር እያደገ የሚሄድ የት/ት ስርአት በዘላቂነት ለመዘርጋት፤እጩ ምሩቃን በእዉቀት፤በክህሎት እና በአመለካከት በየ ምሩቃን ፕሮፋይል የተቀመጠዉን ብቃት ማሟላታቸዉን ማረጋገጥ ስለሚገባ፤በፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የሚመለከታቸዉን የባለ ድርሻ አካላትን በአግባቡ ማሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤እነዚህን መቅደሞች መነሻ በማድረግ ት/ት ሚኒስቴር በከፍተኛ ት/ት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀፅ 95 ንዑስ አንቀፅ 2 እና አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት የከፍተኛ ት/ት የመዉጫ ፈተና መመሪያ ቁጥር 919/2014 አዉጥቶ ወደ ከፍተኛ ት/ት ተቋማት በቁጥር 01/256/306/14 ሀምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም የፃፈዉን ደብዳቤ ሺኚ በማድረግ መላኩ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም ተቋማችን በአሁኑ ወቅት በመደበኛ እና በሳምንቱ መጨረሻ በመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች በአዲሱ ካሪኩለም ያስተማራቸዉ እና የ 2015 ዓ.ም አገራዊ የመዉጫ ፈተና የሚወስዱ ከ 1095 እጩ ተመራቂ ተማሪዎች ለትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት እንዳደረገ ይታወቃል፡፡በዚህም መሰረት የዩኒቨርሲቲዉን የ 2015 ዓ.ም አገራዊ የመዉጫ ፈተናን ስራ ለማሳለጥ ሲባል የትምህርት ሚኒስቴር አቅጣጫን፤የከፍተኛ ት/ት የመዉጫ ፈተና መመሪያ ቁጥር 919/2014 እና ሚኒስቴሩ ያዘጋጃቸዉ የጋራ መድረኮች ምክረ ሀሳብ መነሻ በማድረግ በዩኒቨርሲቲያችን ፕሬዝደንት ጽ/ቤት የሚመራ እና በዋናነት ኮሚቴዎች ማቋቋምና ሀላፊነትን ለይቶ ለመስጠት የሚያስችል “የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ መዉጫ ፈተና ማስፈፀምያ አጭር መዋቅራዊ መመሪያ” እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

# 1. ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ ሚቋቋም

<u>**መግቢያ**</u>፡ ይህ ምዕራፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር መሪነትና አቅጣጫ ሰጪነት በትምህርት ሪፎርም ዉስጥ አንዱ ለሆነዉ የ 2015 ዓ.ም የመዉጫ ፈተና ለመተግበር "የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴ" የማቋቋሚያ ክፍል ነዉ፡፡ ይህ ምዕራፍ ኮሚቴ ከማቋቋም በተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት የሚያካትት ይሆናል፡፡

## 1.2 የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ አብይ ኮሚቴ ትርጉም

<u>**ትርጉም**</u>፡ <u>**የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ፡-**</u> ማለት በዩኒቨርሲቲዉ በ2015 ዓ.ም የት/ት ዘመን መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መረሀ ግብር የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች ለሚሰጠዉ የመዉጫ ፈተና አጠቃላይ ቅድመ ዝግጅትም ሆነ ሌሎች ከመዉጫ ፈተናዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ስራዎች በግንባር ቀደምትነት የሚያከናዉን ሆኖ በዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝደንት የሚመራ ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 1._የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት እና ሃላፊነት**

| ተ.ቁ | የአብይ ኮሚቴዉ አባላት | ሀላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝደንት | ሰብሳቢ |
| 2. | የአካዳሚክ ጉዳዮች እና ምርምር ም/ፕሬዝደንት | ፀሀፊ |
| 3. | የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዝደንት | አባል |
| 4. | የሬጅስትራርና አልሙናይ ዳ/ዳይሬክተር | አባል |
| 5. | ፕሮግራምና ፕሮሞሽን ዳ/ዳይሬክተር | አባል |
| 6. | የላይበራሪ እና ዶክመንቴሽን ዳ/ዳይሬክተር | አባል |
| 7. | የአይ.ሲ.ቲ. ዳ/ዳይሬክተር | አባል |
| 8. | የት/ት ጥራት ማረጋገጥ ዳ/ዳይሬክተር | አባል |
| 9. | የርቀት እና ተከታታይ ት/ት ዳ/ዳይሬክተር | አባል |
| 10. | የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን | አባል |
| 11. | የማህበራዊና ስነ ሰብ ኮሌጅ ዲን | አባል |
| 12. | የህፀተ-ዝናብ ኮሌጅ ዲን | አባል |
| 13. | የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ ዲን | አባል |

## 1.3 የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

1. የት/ት ሚኒስቴር የመዉጫ ፈተና ትግበራ የድርጊት መረሐ ግብርን መነሻ በማድረግ ከዩኒቨርሲቲዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የመዉጫ ፈተናዉን የሚመራበት መመሪያና የድርጊት መረሐ ግብር ያዘጋጃል፤በሰኔት ያፀድቃል።

2. በአይ.ሲ.ቲ፤በላይብራሪ፤በኮሌጅ፤ በት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተናዉን ዉጤታማ እንዲሆን እና በዋናነት ይህንን ስራ ሊያሳልጡ የሚችሉ የተለያዩ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ እንዲሁም ለተጠቀሱት እና ለሚቋቋሙት ኮሚቴዎች የመዉጫ ፈተናዉን በተመለከተ ከት/ት ሚኒስቴር በተሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት በአተገባበሩ እና በቅድመ ዝግጅት ስራዎች ዙሪያ ገለፃ እና ማብራሪ ይሰጣል።

3. በመዉጫ ፈተናዉ ዙሪያ በሚኒስተሩ በኩል አዳዲስ እና የተሻሻሉ ወይም የተለወጡ መመሪያዎች ካጋጠሙ በፍጥነት ለሚመለከተዉ ሁሉ ያደርሳል፤ተፈፃሚነቱንም ያረጋግጣል።

4. ለዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ በመዉጫ ፈተናዉ ዙሪያ አጠቃላይ ግንዛቤ ወይም ኦረንቴሽን በሚከተለዉ አግባብ ከፋፍሎ ይሰጣል፤

   - ☞ አጠቃላይ ለዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ (ለአካዳሚክ እና አስተዳደር ሰራተኞች በሙሉ)
   - ☞ ለመምህራን (በልዩ ሁኔታ ተማሪ እንዲያበቁ በመዉጫ ፈተና ዙሪያ ስልጠና ነክ ኦረንቴሽን ይሰጣል።)
   - ☞ ለተማሪዎች (በ2015 የመዉጫ ፈተናዉን ለሚወስዱ መረሀ ግብር ወጥቶለት በየ ኮሌጃቸዉ ኦረንቴሽን ይሰጣል።)

5. ሁሉንም ኮሚቴዎች በተዋረድ ያሳተፈ የስራ ክፍፍል ይሰጣል፤ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤ይገመግማል፤ይቆጣጠራል እንዲሁም ክፍተት ካለ አፋጣኝ ማስተካከያ እና እርምጃ ይወስዳል።

6. መዉጫ ፈተናዉን የሚሰጡ ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም ኮር ኮምፒተንሲ ማግኘታቸዉና ለመምህራንና ተማሪዎች ማሰራጨታቸዉ ማረጋገጥ፤ክፍተት ካለ ገምግሞ ማስተካከያ ማድረግ፡፡

7. በ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የመዉጫ ፈተናዉን የሚወስዱ ተማሪዎች ሙሉ መረጃ በአግባቡ መጠናከሩ እና ሚኒስቴሩ በጠየቀዉ አግባብ መዘጋጀቱ ያረጋግጣል፡፡

8. ለ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መዉጫ ፈተናዉን በበይነ መረብ ለመስጠት የሚያስችሉ እና ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የተደረጉ ኔትወርክ ኮኔክትድ ኮምፒዉተሮች በተገቢዉ ላብራቶሪ መደራጀታቸዉ ምልከታ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት፡፡

9. በሞዴል ፈተና ዉጤት መሰረት እንዲሁም በመዉጫ ፈተናዉ ብዙ ተማሪዎችን ያሳለፈ ኮሌጅ እና ዲፓርትመንት በአግባቡ በመለየት በቢሮ እና በግለሰብ ደረጃ በአይነቱ ለየት ያለ ሽልማት ይሸልማል፡፡

10. መምህራንን በሚከተለዉ አግባብ ይሸልማል እንዲሁም ተጠያቂ ያደርጋል፤

- ☞ ተማሪዎቹ በመለሱት መልስ በመመርኮዝ ጥያቄዎቹ በአግባቡ የተመለሱለት ኮርስ ባለቤት (መምህር) እዉቅና ይሰጣል፤ይሸልማል፡፡
- ☞ ተማሪዎቹ በመለሱት መልስ በመመርኮዝ ጥያቄዎቹ በአግባቡ ያልተመለሱለት ኮርስ ባለቤት (መምህር) ያልመለሱበትን ምክንያት፤ የት/ት አይነት እና ፀባይ፤የተማሪዎች አለማንበብ፤የማጣቀሻ መፅሀፍት ችግር እና ሌሎች ነባራዊ ሆኔታዎች ከግምት በማስገባት ከተጣራ በኋላ ችግሩ ከመምህሩ ከሆነ አስፈላጊዉን የእርምት እርምጃ የሚወስድ ይሆናል፡፡
- ☞ እነዚህና ሌሎች መዉጫ ፈተናዉን ዉጤታማ የሚያደርጉ ስራዎች ያከናዉናል፡፡

# 2. ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 የኮሌጅ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም

<u>**መግቢያ**</u>፡ በትምህርት ሚኒስቴር ሪፎርም ዉስጥ አንዱ ለሆነዉ የ 2015 ዓ.ም የመዉጫ ፈተና ለመተግበር "በኮሌጅ ደረጃ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴ" የማቋቋሚያ ክፍል ነዉ፡፡ ይህ ምዕራፍ በኮሌጅ ደረጃ የሚቋቋመዉ ኮሚቴ ምን ምን ዝርዝር ተግባራት እንደሚያከናዉን የሚጠቁምና አቅጣጫ የሚሰጥ መሰረታዊ ክፍል ነዉ፡፡

## 2.2 በኮሌጅ ደረጃ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ትርጉም

<u>**ትርጉም**</u>፡ **በኮሌጅ ደረጃ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ፡-** ማለት በዩኒቨርሲቲዉ በ2015 ዓ.ም የት/ት ዘመን መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ለሚሰጠዉ የመዉጫ ፈተና በኮሌጅ ደረጃ አጠቃላይ ቅድመ ዝግጅትም ሆነ ሌሎች ኮሌጁ ዉስጥ ከመዉጫ ፈተናዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ስራዎች የሚያከናዉንና በኮሌጅ ዲኑ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 2. በኮሌጅ ደረጃ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት እና ሃላፊነት**

| ተ.ቁ | የኮሚቴዉ ተሳታፊ አባላት | ሀላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | የኮሌጁ ዲን | ሰብሳቢ |
| 2. | በኮሌጅ የተመረጠ 1 የት/ት ክፍል ሀላፊ | ፀሀፊ |
| 3. | መዉጫ ፈተናዉን የሚሰጡ ት/ት ክፍል ሀላፊዎች | አባል |
| 4. | 1 ወንድ የኮሌጁ ተማሪዎች ተወካይ | አባል |
| 5. | 1 ሴት የኮሌጁ ተማሪዎች ተወካይ | አባል |

## 2.3 በኮሌጅ ደረጃ የሚቋቋመዉ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

1. የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴን መመሪያ እና የት/ት ሚኒስቴር የመዉጫ ፈተና ትግበራ የድርጊት መረሐ ግብርን መነሻ በማድረግ ከኮሌጁ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የመዉጫ ፈተናዉን የሚመራበት መመሪያ እና የድርጊት መረሐ ግብር ያዘጋጃል፤በኮሌጅ ካዉንስል አፀድቆ ወደ ስራ ያስገባል፡፡

2. የመዉጫ ፈተናዉ በኮሌጁ ደረጃ ዉጤታማ እንዲሆን እና በዋናነት ይህንን ስራ ሊያሳካ የሚችል ኮሚቴ በት/ት ክፍል ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡
3. በት/ት ክፍል ደረጃ ለሚቋቋሙት ኮሚቴዎች የመዉጫ ፈተናዉን በተመለከተ ከዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴ በተሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት በአተገባበሩ እና በቅድመ ዝግጅት ስራዎች ዙሪያ ገለፃ እና ማብራሪያ ይሰጣል፡፡
4. በመዉጫ ፈተናዉ ዙሪያ ከዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና የሚመራ ኮሚቴ በኩል አዳዲስ እና የተሻሻሉ ወይም የተለወጡ መመሪያዎች ካጋጠሙ በፍጥነት በት/ት ክፍል ደረጃ ለሚቋቋመዉ ኮሚቴ ያደርሳል፤ተፈፃሚነቱንም ያረጋግጣል፡፡
5. በት/ት ክፍል ደረጃ በሁሉም መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች ስር ፈጣን የሆነ የመረጃ መለዋወጫ መንገድ መዘርጋታቸዉን ያረጋግጣል፤ክፍተት ካለ በፍጥነት ያርማል፡፡
6. በሁሉም መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ ሞዳሊቲ በኮሌጁ ስር መዉጫ ፈተናዉን የሚሰጡ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች ኮር ኮምፒተንሲ ማግኘታቸዉና ለመምህራንና ተማሪዎች ማሰራጨታቸዉ ማረጋገጥ፤ክፍተት ካለ ገምግሞ ማስተካከያ ማድረግ፡፡
7. በኮሌጁ ስር በ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የመዉጫ ፈተናዉን የሚወስዱ ተማሪዎች ሙሉ መረጃ በአግባቡ መጠናከሩ እና ከሬጅስትራር ቢሮ ጋር ተመሳሳይ የተማሪዎች መረጃ መኑሩን ያረጋግጣል፡፡
8. በ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መዉጫ ፈተናዉን በብቃት ለተወጡት ት/ት ክፍሎች፤መምህራን እና የኮሚቴ አባላት እንዲሁም የሚቀጡትም ጭምር በዩኒቨርሲቲዉ ደረጃ ለማሸለም የሚያስችለዉን መረጃ አጠናክሮ ለአብይ ኮሚቴዉ በሰዐቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

☞ **እነዚህና ሌሎች በኮሌጅ ስር መዉጫ ፈተናዉን ዉጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡**

# 3. ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 የት/ት ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም

<u>መግቢያ</u>፡ የ 2015 ዓ.ም የመዉጫ ፈተና ለመተግበር እና ዉጤታማ ለመሆን ትልቁን ስራ የሚያከናዉነዉ እና የሚያስፈፅመዉ የት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋሚያ ምዕራፍ ነዉ። ኮሚቴዉ ከማቋቋም በዘለለ ዝርዝር ተግባራትም የሚጠቀሱበት ክፍል ነዉ።

## 3.2 በት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ትርጉም

<u>ትርጉም</u>፡ **በት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ፡-** ማለት በዩኒቨርሲቲዉ በ2015 ዓ.ም የት/ት ዘመን መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞች በመጀመሪያ ዲግሪ ለሚሰጠዉ የመዉጫ ፈተና በት/ት ክፍል ደረጃ አጠቃላይ ቅድመ ዝግጅትም ሆነ ሌሎች ትምህርት ክፍሉ ዉስጥ ከመዉጫ ፈተናዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን በርካታ ስራዎችን የሚያከናዉን እና በት/ት ክፍሉ ሃላፊ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ በኮሌጅ ደረጃ ለሚቋቋመዉ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል።

**ሰንጠረዥ 3._በት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት እና ሃላፊነት**

| ተ.ቁ | የኮሚቴዉ ተሳታፊ አባላት | ሀላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | የትምህርት ክፍሉ ሃላፊ | ሰብሳቢ |
| 2. | በት.ት ክፍሉ የተመረጠ 1 ነባር መምህር | ፀሀፊ |
| 3. | ልምድ ያላቸዉ ነባር መምህራን | አባል |
| 4. | 1 ወንድ የክፍል ተወካይ ተማሪ | አባል |
| 5. | 1 ሴት የክፍል ተወካይ ተማሪ | አባል |

## 3.3 የት/ት ክፍል ደረጃ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

3.2.1 የመዉጫ ፈተናዉን ስራ ሊያሳካ የሚችል ኮሚቴ በት/ት ክፍል ደረጃ ከላይ በተቀመጠዉ ሰንጠረዥ መሰረት አቋቁሞ ወደ ስራ ይገባል።

3.2.2 ሀገራዊ የመዉጫ ፈተና የድርጊት መረሐ ግብርን መነሻ በማድረግ ከት/ት ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የመዉጫ ፈተናዉን የሚመራበት የድርጊት መረሐ ግብር አዘጋጅቶ ወደ ስራ ይገባል፡፡

3.2.3 በት/ት ክፍል ደረጃ በሁሉም መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞች በመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች መካከል ፈጣን የሆነ የመዉጫ ፈተና መረጃ መለዋወጫ መንገድ መዘርጋታቸዉን ያረጋግጣል፤ክፍተት ካለ በፍጥነት ይዘረጋል፡፡

3.2.4 በት/ት ክፍሉ ስር የሚገኙ መምህራን እና ተማሪዎች ኮር ኮምፒተንሲ (ለፈተናዉ የተለዩ ኮርሶች) በአግባቡ ማግኘታቸዉን ያረጋግጣል፡፡

3.2.5 መዉጫ ፈተናዉን በተመለከተ በተዋረድ የሚያገኛቸዉን ህጋዊ መረጃዎች ብቻ ለት/ት ክፍሉ መምህራን እና ተማሪዎች በወቅቱ ያደርሳል፡፡

3.2.6 በት/ት ክፍሉ ስር በ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የመዉጫ ፈተናዉን የሚወስዱ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ሙሉ መረጃ በአግባቡ ያደራጃል እንዲሁም ከሬጅስትራር ቢሮ ጋር ተመሳሳይ የተማሪዎች መረጃ መኑሩን ያረጋግጣል፡፡

3.2.7 በኮር ኮምፒተንሲ (ለፈተናዉ በተለዩ ኮርሶች) መሰረት ቲቶሪያል የሚሰጡ ልምድ እና ብቃት ያላቸዉን መምህራንን ይመርጣል፡፡

3.2.8 ከመደበኛዉ ክፍለ ጊዜ እንዳይጋጭ አድርጎ ቲቶሪያል የሚሰጥበትን መንገድ ወይም ክፍለ ጊዜ ያመቻቻል፡፡

3.2.9 ተማሪዎችን ለዉጤት የሚያበቁ ስታንዳርድ የንባብ መረጃዎች/ማቴሪያሎች ልምድ እና ብቃት ባላቸዉ መምህራን ተዘጋጅቶ በተዘረጋዉ መረጃ ቋት በኩል ለተማሪዎች በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፤እንዲሁም ማቴሪያሎቹ ለላይብረሪ ኮሚቴ በወቅቱ ያስረክባል፡

3.2.10 ከቲቶሪያል ጎን ለጎን ኮር ኮምፒተንሲ (ለፈተናዉ የተለዩ ኮርሶችን) የሚመጥን የምርጫ ጥያቄ ወይም የሞዴል ጥያቄ ተዘጋጅቶ ተማሪዎቹ እንዲመዘኑ ያደርጋል፡፡

3.2.11 የሞዴል ፈተና ዉጤትን መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን ክፍተት በመለየት በፍጥነት መሙላት እንዲሁም፤የዉጤቱ ግብረ መልስ ለኮሌጁ የመዉጫ ፈተና አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3.2.12 ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት በት/ክፍሉ ለመመረቅ በካሪኩለም የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ የመዉጫ ፈተናዉ እንደአንድ መስፈርት ስለተቀመጠ በአንድ ገፅ መግለጫ የመዉጫ ፈተናዉ የመመረቂያ ዋንኛ መስፈርት መሆኑ ተፅፎና ስታምፕ በማድረግ ከት/ክፍሉ ካሪኩለም ጋር አብሮ መጠረዙ ያረጋግጣል፤ካልተሰራም በፍጥነት እንዲሰራ ያደርጋል፡፡

3.2.13 ለሴቶች እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ (በዉጤት፤በአካል ጉዳት እና በሌሎች) ተማሪዎች ቲቶሪልና ሌሎች ተመሳሳይ ድጋፍ እንዲያገኙ ያመቻቻል፡፡

3.2.14 በመዉጫ ፈተናዉ ዙሪያ ተከታታይነት ያለዉ ኦረንቴሽን ለትምህርት ክፍሉ ተማሪዎች እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

3.2.15 በ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መዉጫ ፈተናዉን በብቃት በመወጣት ከፍተኛ ዉጤት ያስመዘገቡ መምህራንና እና የኮሚቴ አባላት እንዲሁም የሚቀጡትም ጭምር በዩኒቨርሲቲዉ ደረጃ ለማሸለም የሚያስችለዉን መረጃ አጠናክሮ ለኮሌጅ እና ለአብይ ኮሚቴዉ በሰዐቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

**3.2.16 እነዚህና ሌሎች በት/ት ክፍሉ ስር መዉጫ ፈተናዉን ዉጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡**

# 4. ምዕራፍ አራት

## 4.1 የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም

<u>**መግቢያ**</u>፡ የ 2015 ዓ.ም የመዉጫ ፈተና ለመተግበር እና ዉጤታማ ለመሆን ከፋሲሊቲ (ከተማሪዎች አቅም ግንባታ፤ ኮምፒዉተር፤መብራት እና ኔትዎርክ) ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ስራዎችን የሚያከናዉን እና የሚያስፈፅም የአይ.ሲ.ቲ ክፍል ኮሚቴ ማቋቋሚያ ምዕራፍ ነዉ፡፡ ኮሚቴዉ ከማቋቋም በዘለለ ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራትም የሚገለፅበት ክፍል ነዉ፡፡

## 4.2 የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ትርጉም

<u>**ትርጉም**</u>፡ **የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ፡-** ማለት በዩኒቨርሲቲዉ በ2015 ዓ.ም የት/ት ዘመን መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞች ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ለሚሰጠዉ የመዉጫ ፈተና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ አጠቃላይ ከፋሲሊቲ ጋር ተያያዥነነት ያላቸዉ ስራዎች የሚያከናዉን እና በአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲዉ ወዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 4._የአይ.ሲ.ቲ ክፍል ኮሚቴ አባላት እና ሃላፊነት**

| ተ.ቁ | የኮሚቴዉ ተሳታፊ አባላት | ሀላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | የአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | ሰብሳቢ |
| 2. | ከፍተኛ ዳታ ቤዝ ባለሙያ | ፀሀፊ |
| 3. | ሁለት የኔትዎርክ ባለሙያ | አባል |
| 4. | ሁለት የጥገና ባለሙያ | አባል |

### 4.3 የአይ.ሲ.ቲ ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

1. በስታንዳርዱ መሰረት ለመዉጫ ፈተናዉ ማስፈፀሚያ የሚዉሉ ኮምፒዉተሮች ዝግጁ ያደርጋል (ቢያንስ 300 ኮምፒዉተሮች እና 10 ላብራቶሪ ክፍሎች፣ማለት 1:30)።

2. ከላይ የተጠቀሱት ኮምፒዉተሮች በላብራቶሪ (ኮምፒዉተር ላብ) ተደራጅተዉ እና ከኔትዎርክ ጋር በማገናኘት ለበየነ መረብ ፈተና ዝግጁ መሆናቸዉን ያረጋግጣል።

3. ለኮምፒዉተር ላብራቶሪ በቂ የሀይል አቅርቦት መኖሩን ከማረጋገጥ ባለፈ፣ፈተናዉ በሚሰጥበት ወቅት የሀይል መቆራረጥ ሊያጋጥም ስለሚችል፣ላብራቶሪዎቹ ከአዉቶማቲክ ጄኔሬተሮች ጋር በአስተማማኝ ሁኔታ በገናኝታቸዉን ያረጋግጣል።

4. በመዉጫ ፈተና እና በአጠቃላይ ላብራቶሪያ አጠቃቀም ዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር በእያንዳንዱ ኮምፒተር ላብ አንድ ባለሙያ በመመደብ ሁሌም ኮምፒዉተር ላቡ ያለምንም እንከን ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋል።

5. ልዩ ክፍለ ጊዜ በማዘጋጀት መዉጫ ፈተናዉን ለሚወስዱ ተማሪዎች በኦንላይን ፈተና አሰጣጥ እና አፈታተን ዙሪያ ተግባር ተኮር ስልጠና በመስጠት ከዋናዉ ፈተና በፊት ተማሪዎችን ዝግጁ ያደርጋል።

**☞እነዚህና ሌሎች በክፍሉ ስር መዉጫ ፈተናዉን ዉጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል።**

# 5. ምዕራፍ አምስት

## 5.1 የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል የመዉጫ ፈተና ኮሚቴ ማቋቋም

<u>**መግቢያ**</u>፡ የ 2015 ዓ.ም የመዉጫ ፈተና አስመልክቶ ከተማሪዎች ንባብ እና ዝግጅት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ስራዎችን የሚሰራ እና የሚያስፈፅም የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል ኮሚቴ ማቋቋሚያ ምዕራፍ ነዉ፡፡ ኮሚቴዉ ከማቋቋም በተጨማሪ ተግባራትም የሚገለፅበት ክፍል ነዉ፡፡

## 5.2 የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል የመዉጫ ኮሚቴ ትርጉም

<u>**ትርጉም**</u>፡ **የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል ኮሚቴ፡** ማለት በዩኒቨርሲቲዉ በ2015 ዓ.ም የት/ት ዘመን መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞች ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ለሚሰጠዉ የመዉጫ ፈተና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ አጠቃላይ ከንባብ ጋር ተያያዥነነት ያላቸዉ ስራዎች የሚያከናዉን እና በላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲዉ ወዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 4._የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል ኮሚቴ አባላት እና ሃላፊነት**

| ተ.ቁ | የኮሚቴዉ ተሳታፊ አባላት | ሀላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | ሰብሳቢ |
| 2. | የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር | ፀሀፊ |
| 3. | ሁለት ኮኦርዲኔተሮች | አባል |
| 4. | አምስት አቴንዳንት (ተቆጣጣሪዎች) | አባል |

## 5.3 የላይብራሪ እና ዶክመንቴሽን ክፍል ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

1. ላይብራሪ ዉስጥ የሚገኙ ለመዉጫ ፈተናዉ ዝግጅት ሊዉሉ የሚችሉ የንባብ ማቴሪያሎች ተለይተዉ በአመቺ ሁኔታ እንዲደራጁ ያድርጋል፡፡

2. ለመዉጫ ፈተናዉ የተለዩ ኮርሶች ከሁሉም ትምህርት ክፍሎች በማሰባሰብ እንዲሁም በማባዛት እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡

3. በመዉጫ ፈተናዉ ተማሪዎችን ስኬታማ ሊደርጉ ይችላሉ ተብለዉ በየ ትምህርት ክፍሉ የተዘጋጁ መፅሀፎች፤ሞጁሎች፤ሀንዳዉቶች እና ሌሎች ማቴሪያሎች ከት/ት ክፍል ጋር በመተባበር ተባዝተዉ በተገቢዉ ቦታ እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡

4. በተቻለ አቅም የመዉጫ ፈተናዉን የሚወስዱ ተማሪዎች የሚያጠኑበት ልዩ የማንበቢያ ቦታ እንዲዘጋጅ ደርጋል፤ንፅህናዉን እና የቦታዉ ወቅታዊ ሁኔታ በየ ጊዜዉ ይከታተላል፡፡

5. የመዉጫ ፈተናዉን የሚወስዱ ተማሪዎች በተለየ ሁኔታ በየትምህርት ክፍሉ መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ ተዘጋጅቶ የንባብ ሂደታቸዉን በመከታተል ቁጥራዊ መረጃ ለዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና አብይ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

☞እነዚህና ሌሎች በክፍሉ ስር መዉጫ ፈተናዉን ዉጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

# 6. ምዕራፍ ስድስት

## 6.1 ማጠቃለያ

የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ት/ት የመዉጫ ፈተና መመሪያ ቁጥር 919/2014 እና በተለያዩ መድረኮችና ማህበራዊ ሚዲያዎች በትምህርት ዘመኑ ከያዛቸዉ አጀንዳዎች አንዱና ዋንኛዉ የ 2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ የመዉጫ ፈተና መተግበር እና ዉጤታማ መሆን እንደሆነ አሳዉቋል፡፡

ስለሆነም ዩኒቨርሲቲያችን ዉስጥ የሚገኝ ከላይኛ እስከ ታችኛዉ መዋቅር እንዲሁም በአጠቃላይ በአከዳሚክም ሆነ በአስተዳደር ስር ያለ ማህበረሰብ በተቋማችን የሚሰጠዉን የ 2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ የመዉጫ ፈተና ዉጤታማ እንዲኖንና ብዙ ብቁ ምሩቃን እንድናፈራ ለነገ ሳይል የሚሰራዉ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡

**<u>ልዩ መልዕክት</u>**

**ይህ መመሪያ በየጊዜዉ በትምህርት ሚኒስቴር፤በዩኒቨርሲቲዉ ከፍተኛ አመራር እና በሚመለከተዉ አካል ማሻሻያ የሚደረግበት ሆኖ፤ በሰኔት ፀድቆ በዩኒቨርሲቲዉ ከፍተኛ አመራር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የዩኒቨርሲቲዉ የመዉጫ ፈተና ማስፈፀምያ መዋቅራዊ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡**

------------------------------------ ---------------------------------------

ኢ/ር አብዲፈታህ አህመድ (ፕሬዝደንት)

ረ/ፕሮፌሰር አብዲሰላም አብዲላሂ (የአ/ጉ/ም/ም/ፕሬዝደንት)